ጦርና ፡ ጋሻውን ፡ ይዞ ፡ « ልጄ ፡ በሕይወት ፡ ላግኝህ ! የአይኔ ፡
አበባዬ ! » ብሎን ፡ ወጣ ።

አባቴ ፡ ከሌሎች ፡ የጦር ፡ ጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ጦሩ ፡
ሜዳ ፡ ገሠገሠ ። የጦርነቱ ፡ ሥፍራ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ኪሎ ፡ ሜት
ር ፡ ያህል ፡ ይርቅ ፡ ስለነበረ ፡ በእግር ፡ የአሥራ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡
መንገድ ፡ ነበር ። እምዬና ፡ እኔ ፡ እንዲሁም ፡ አያቴ ፡ አባቴን ፡
ሸኝተን ፡ ወደ ፡ ቤታችን ፡ ከተመለስን ፡ በኋላ ፡ ላንድ ፡ ሁለት ፡
ሰዓት ፡ ያህል ፡ ቁጭ ፡ ብለን ፡ በኀዘን ፡ መልክ ፡ እርስ ፡ በርሳችን፡
ተፋጠጥን ፣ አያቴ ፡ ወለተ ፡ ወልድ ፡ « ምነው ፡ ልጄ ! አያድር
ገውና ፡ ቀብሮ ፡ እንደተመለሰ ፡ ሰው ፡ ቅጥ ፡ አጣን ! እረ ፡ ተነሽ፡
እስኪ ፡ ቡና ፡ አፍይና ፡ ጉዞህን ፡ ያቃናልህ ፡ እንበለው ፣ ኤፍሬም ፡
አንተም ፡ ተነስ ፡ እስኪ ፡ ወኃ ፡ ቀድተህ ፡ አምጣ ፡ » ብለው ፡
ለያንዳንዳችን ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጡን ። እንግዲህ ፡ አባቴ ፡ የለምና ፡
ከነበርነው ፡ ሥስታችን ፡ እንደተመቸን ፡ ትዕዛዝ ፡ መስጠት ፡ የም
ንችል ፡ መሆናችንን ፡ ተገንዝበኩና ፡ እኔም ፡ ሥራ ፡ ማከፋፈሉ ፡
ውስጥ ፡ ገባሁ ። « እማማ ፡ ትልቋ ፡ ቡናውን ፡ ይቁሉ ፡ እማዬ ፡
ወሃ ፡ ትቅዳ ፡ እኔ ፡ እንጨት ፡ ለቃቅሜ ፡ ላምጣ ፡ » ስል ፡ ባሳ
ስብ ፡ ተቃራኒ ፡ አሳብ ፡ አልገጠመኝም ። ሁላችንም ፡ ሥራ ፡ ተከ
ፋፍለን ፡ ቡናው ፡ ተፈላ ፣ ጐረቤቶችን ፡ ጥራ ፡ ተብዬ ፡ እየዞ
ርኩ ፡ « ቡና ፡ ጠጡ ፡ ተብላችኋል ፡ » እል ፡ ጀመር ። ወንዶቹ ፡
ወደ ፡ ጦርነት ፡ ሄደዋልና ፡ የሴቶች ፡ ቁጥር ፡ በጣም ፡ በረከተ ።
እንደገቡ ፡ ሁሉም ፡ ስለባሎቻቸው ፡ የሚያወሩ ፡ መሰሉና ፡ ካንዳ
ንድ ፡ ስኒ ፡ ቡና ፡ በኋላ ፡ ወሬው ፡ ተለወጠ ፣ ጨዋታው ፡ ደራ ።
ሁለተኛ ፡ ሶስተኛ ፡ ሲባል ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ጠፍቶ ፡ ቡና
አጣጮች ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሄዱ ። ከዚያ ፡ ወዲያማ ፡ በየቤቱ ፡
ቡናው ፡ ቀጠለና ፡ ጫጫታው ፡ በመድረክ ፡ ላይ ፡ እንደሚታይ ፡
ቲያትር ፡ ያስገርም ፡ ጀመር ። በየምክንያቱ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡
ያልሄዱት ፡ ሰዎች ፡ ከሴቶች ፡ ጋር ፡ በየቤቱ ፡ እየዞሩ ፡ ቡና ፡
ያጣጡ ፡ ስለነበረ ፡ ሴቶቹ ፡ «ከኛም ፡ የማይሻሉ ፡» እያሉ ፡ ስለአ



ሽሚጠጧቸው ፡ ለቡና ፡ አብረው ፡ መዞሩን ፡ ተዉት ፣ ሴቶቹ ፡
ብቻቸውን ፡ ቀጠሉና ፡ የቡናው ፡ ፋብሪካ ፡ እየተስፋፋ ፡ ሄደ ።

ችግሩ ፡ የበረታው ፡ በየቤቱ ፡ የተጣልነው ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡
ነበር ። ምግብ ፡ አይሠራም ፡ ቢሠራም ፡ ለግብር ፡ ይውጣ ፡ ነው ፣
ሽሮው ፡ ጨው ፡ አያውቅ ፡ በርበሬ ፡ ምኑ ፡ ቅጡ ! ልጁ ፡ ሁሉ ፡
ማከክ ፡ ጀመረ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ የአሥር ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ብሆንም ፡ የእ
ምዬንና ፡ እሷን ፡ የመሰሉትን ፡ ጓደኞችዋን ፡ አድራጐት ፡ በጣ
ም ፡ እታዘብ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ብናገር ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ድምጼ ፡
ሊሰማ ፡ ስለማይችል ፡ ጠቅላላው ፡ ሰውነቴ ፡ የኀዘን ፡ ምልክት ፡
እንዲያሳይልኝ ፡ ከማድረግ ፡ በቀር ፡ ከመናገር ፡ እቆጠብ ፡ ነበር።
አያቴም ፡ የሰውን ፡ እጅ ፡ አይታ ፡ የምትኖር ፡ ያልተሳካላት ፡
ፍጥረት ፡ ስለነበረች ፡ ያየችውን ፡ ሁሉ ፡ በዝምታ ፡ ከማሳለፍ ፡
ተናግራ ፡ የምታስገኘው ፡ ውጤት ፡ አልነበረም ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አባቴ ፡ ከቤት ፡ በወጣ ፡ በአሥራ ፡
አራተኛው ፡ ለሊት ፡ በሕልሜ ፡ ጥርሶቼ ፡ ወልቀው ፡ ድምጼን ፡
አጉልቼ ፡ ሳለቅስ ፡ እምዬ ፡ ቀሰቀሰችኝ ። « በስመ ፡ አብ ፡ ወወ
ልድ ! ምነው ! ምነው ! » ብላ ፡ ደንግጣ ፡ « ምን ፡ ሆነሃል ፡ »
ስትለኝ ፡ እኔም ፡ « አንድ ፡ ነገር ፡ ጥርሶቼን ፡ አውልቆብኝ ፡ ነው፡
እማዬ ! » አልኳት ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ አያቴና ፡ እምዬ ፡ ለሕልሜ
ከባድ ፡ ትርጉም ፡ ሰጥተው ፡ ያልቅሱ ፡ ይጨነቁ ፡ ጀመር ። ለሊ
ቱ ፡ ነግቶ ፡ በሕልም ፡ የወለቁብኝ ፡ ጥርሶቼ ፡ የትኞቹ ፡ እንደነ
በሩ ፡ ቢጠይቁኝ ፡ ከፊት ፡ ጥርሶቼ ፡ የላይኛው ፡ ክፍል ፡ መሆና
ቸውን ፡ ገለጽኩላቸውና ፡ ድንጋጤአቸው ፡ እየከበደ ፡ ሄደ ።
እኔም ፡ « በሕልሜ ፡ ጥርሶቼ ፡ ቢነቀሉ ፡ በውኔ ፡ አሉ ፡ ምን ፡
ያስለቅሳቸዋል ፡» እያልኩ ፡ ልገረም ፡ እንጂ ፡ ለካስ ፡ እነሱ ፡ የተረ
ጐሙት ፡ በአባቴ ፡ ሞት ፡ ነበር ! ሕልሜ ፡ የጠንቋይ ፡ ወሬ ፡ ሆኖ
ባቸው ፡ ሲያብሰለስሉ ፡ ሰነበቱና ፡ ከዚያም ፡ በየቦታው ፡ እየተ
ዘዋወሩ ፡ የአርበኞችን ፡ ሁናቴ ፡ ይጠይቁ ፡ ጀመር ፡ ለጊዜው ፡
ምንም ፡ ወሬ ፡ አጡ ።

በዚሁ ፡ አሳብ ፡ ስንተራመስ ፡ እያለን ፡ መንግሥት ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ የሞቱትን ፡ ጀግኖች ፡ ልጆች ፡ ባዳሪነት ፡ ተቀብሎ ፡ ያስተምራል ፡ ሲባል ፡ ሰማች ፡ በጣም ፡ ተደሰተች ። ውላ ፡ ሳታድር ፡ ለባላባቱ ፡ አመልክታ ፡ ባላባቱም ፡ እምዬን ፡ ለመርዳት ፡ ባስቸኳይ ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ ተጻጽፎ ፡ በአስራ ፡ አንድ ፡ ዓመቴ ፡ ባዳሪነት ፡ ት/ ቤት ፡ ልገባ ፡ ቻልኩ ። እምዬም ፡ ወደ ፡ ዘመዶችዋ ፡ ሄዳ ፡ ከሰነበተች ፡ በኋላ ፡ ጎጆአችን ፡ እንዳይፈርስና ፡ የደሀ ፡ ንብረታችን ፡ እንዳይነጠቅ ፡ የወንድሙዋን ፡ ልጅ ፡ ይዛ ፡ ተመልሳ ፡ ከስድስት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ የብቸኝነት ፡ ኑሮዋን ፡ ጀመረች ። እኔ ፡ ትምህርቴን ፡ ቀጠልኩ ። አንድም ፡ ቀን ፡ እንድለያት ፡ የማትፈልገው ፡ እናቴ ፡ ሳላያት ፡ አራት ፡ አመት ፡ ቆየሁ ። ትምህርት ፡ ቤት ፡ በገባሁ ፡ ልክ ፡ በስምንተኛው ፡ ወር ፡ ለእናቴ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ደብዳቤ ፡ በጫጭሬ ፡ በሰው ፡ ሰደድኩላት ።

« ለክብርት ፡ እናቴ ፡ እምዬ ፡ የዓይኔ ፡ አበባ ፡ አምላክ ፡ ጤናሽን ፡ ጠብቆ ፡ ያቆይልኝ ፡ እንደምን ፡ አለሽ ? እኔ ፡ ደህና ፡ ነኝ ፤ በትምህርትም ፡ ጎብዤለሁ ፡ የኔታ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ልጅ ፡ እያሉ ፡ ይመርቁኛል ፡ ባይኔ ፡ ሥጋ ፡ ይግጠመን ፤ አሜን ፡ ያንቺው ፡ ልጅሽ ፡ ኤፍሬም ፡ ወንድ ፡ ይፍራው ፡ » የሚል ፡ ነበር ።

እምዬም ፡ ገና ፡ ደብዳቤውን ፡ እንደተቀበለች ፡ የሚያነብላትን ፡ ሰው ፡ ፍለጋ ፡ የሦስት ፡ ሰዓት ፡ መንገድ ፡ ሄዳ ፡ አንድ ፡ ቄስ ፡ አገኘችና ፡ « እባክዎን ፡ አባቴ ፡ ይህንን ፡ አንብበሁ ፡ ምን፡ እንደሚል ፡ ግለጡልኝ ፡ » ብላ ፡ ብትለምናቸው ፡ « ለጊዜው ፡ ሥራ ፡ አለብኝና ፡ እስኪ ፡ እስከዚያው ፡ ድረስ ፡ ወለቴን ፡ ትንሽ ፡ ሥራ ፡ እርጂት ፡ » ብለው ፡ የድግሥ ፡ አሻሮ ፡ እንድትፈጭ ፡ አዘዟት ። ደኃ ፡ በየሄደበት ፡ የጉልበት ፡ ሥራ ፡ ይከተለዋልና ፡ ተከትሏት ፡ የሄደው ፡ ድኅነቷ ፡ አሻሮ ፡ እንድትፈጭ ፡ አድርጓት ፡ ለጉዞ ፡ የወሰደባትን ፡ ያህል ፡ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ የጉልበት ፡



ሥራ ፡ አባን ፡ ካገለገለች ፡ በኋላ ፡ ወረቀቱን ፡ አንብበውላት ፡ ተመለሰች ። ስትመለስም ፡ እኔ ፡ ልጅዋ ! የድሀ ፡ ቅርሷ ፡ በጻፍኩላት ፡ ወረቀት ፡ ደስታዋ ፡ ከልብ ፡ አልፎ ፡ አንጀቷ ፡ በተስፋ ፡ ርሶ ! የመንገዱን ፡ ድካም ፡ ሳታስተውል ፡ ወደ ፡ ጎጆዋ ፡ ደረሰች ። ጥቂት ፡ ከሰነበተችም ፡ በኋላ ፡ እኔ ፡ ተምሬ ፡ ቀን ፡ እስካወጣላት ፡ ድረስ ፡ የዕለት ፡ መኖን ፡ በማጣት ፡ የምትጐሳቆል ፡ መሆኗን ፡ እንጂ ፡ ጤንነቷ ፡ ምንም ፡ ያልታወከ ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ አስጽፋ ፡ ላከችልኝ ። ወረቀቱን ፡ ማስጻፊያ ፡ በበኩሉ ፡ የጉልበት ፡ ሥራ ፡ የጠየቃት ፡ መሆኑን ፡ ተረዳሁ ።

ከዚያ ፡ ወድያ ፡ እምዬ ፡ እንዳለችው ፡ ተምሬ ፡ ቀን ፡ እንዳወጣላት ፡ ከመመኘት ፡ በቀር ፡ በየጊዜው ፡ ደብዳቤ ፡ እየጻፍኩ ፡ በመላክ ፡ በጉልበት ፡ ሥራ ፡ ላደክማት ፡ ባለመፈለጌ ፡ ሁለተኛ ፡ አልጻፍኩላትም ። ደብዳቤዎቼንም ፡ ባየች ፡ ቁጥር ፡ እንድትባባ ፡ አልፈለግሁም ።

በአሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመቴ ፡ ገና ፡ አራተኛ ፡ ክፍል ፡ ሆኜ ፡ እምዬ ፡ በጠና ፡ ታምማ ፡ « ልጄን ፡ ሳላይ ፡ መሞቴ ፡ ነው ፡ » እያለች ፡ በማልቀስ ፡ ጎረቤቱን ፡ ሁሉ ፡ አስቸገረችና ፡ በበጅሮንድ ፡ አደፍርሰው ፡ አማካይነት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተላከብኝ ። ሲነገረኝ ፡ እንዳልደነግጥ ፡ ብዙ ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲደረግ ፡ አደራ ፡ አለች ። መልክተኛው ፡ አራት ፡ ቀን ፡ በሙሉ ፡ በበቅሎ ፡ ተጉዞ ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ ደረሰ ። ገና ፡ ሳየው ፡ ተሸበርኩ ። የምናገረውን ፡ እስከማጣት ፡ ተርበትብቼ ፡ ሲያየኝ ፡ እሱም ፡ ደነገጠ ። « ምን ፡ ነካህ ? ለምን ፡ ደነገጥህ ? አለኝ ። » እኔም ፡ « እኔ ፡ እንጃ ! ብቻ ፡ ገና ፡ ሳይህ ፡ ላብ ፡ አሰመጠኝ ፤ ለመሆኑ ፡ እምዬ ፡ ደህና ፡ ነች ? » ስል ፡ ጠየቅሁት ። « በጣም ፡ ደህና ፡ ነች ፡ ግን ፡ ናፍቆኛልና ፡ ካላየሁት ፡ ብላ ፡ ጎረቤቱን ፡ ሁሉ ፡ ግራ ፡ አጋባችው ፤ ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈቃድ ፡ ጠይቀህ ፡ ብትሄድና ፡ ብታይህ ፡ » ሲል ፡ መለሰልኝ ። ከፊተኛው ፡ ይበልጥ ፡ በመደንገጥ ፡ « ምን ፡ ልታሰማኝ ፡ ፈልገህ ፡ ይሆን ? » በማለት ፡ ወደሱ ፡

